# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ ―ሠራተኛ፡ ገበሬ፡ ነጋዴ፡ ወታደር፡ ምሁር― መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

ቁጥር 1 ቀን 14/12/66


## የእንቅስቃሴው ባለቤት ሰፊው ሕዝብ ነው፡፡

የሰው ልጅ ታሪክ የትግል ውጤት ነው፡፡ ትግሉ ከፍጥረት ጋር ነው፡፡ ሰው ራሱ የፍጥረት ክፍል ሆኖ ከፍጥረት ጋር ዝንተአለም የማያቋርጥ ትግል ያደርጋል፡፡ የመላወጥ የማደግ የመሻሻል መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት ሲል ፍጥረትን መለወጥ ግዴታው ነው፡፡ ዋናውና እውነተኛው የሰው ልጅ ታሪክ ይህ ሲሆን፡ አሁን ታሪክ በመባል የሚታወቀውና በታሪክ መፅሀፍት ውስጥ የምናነበው ግን የታሪክ አንድ ትንሽ ክፍል ነው፤ ለዚያውም በተዛባ መንገድ የቀረበ የመደቦች ታሪክ ነው፡፡ አንደኛው መደብ ወጥቶ ወርዶ ወዙን አንጠፍጥፎ የፈጠረውን ሃብት፡ ሌላው መደብ በሃይል በመጨቆን ይቀማዋል፤ የላቡን ፍሬ ይበዘብዘዋል፤ ይዘርፈዋል፡፡ አሁን ታሪክ በሙሉ የሚጠራው የሰው ልጅ እርስበርሱ የሚያደርገው የመደቦች ትግል ነው፡፡ በኢትዮጵያም ታሪክ የሚባለው ባድርባዮች የተፃፈ የጨቋኝና የበዝባዥ ነገስታት ውዳሴ እንጂ የመደቦች ትግል፡ የሕዝብ ታሪክ ባለመሆኑ ከእውነተኛው የሰው ልጅ ታሪክ ምን ያህል ርቀን እንደምንገኝ ለመገመት የሚያዳግት አይመስለም፡፡

ታሪኩ በትክክል ባይፃፍም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማናቸውም የአለም ሕዝብ ታሪክ እሰው በጨቋኝና በተጨቋኝ፡ በበዝባዥና በተበዝባዥ፡ በተቀምጠባሎችና በሃብት ፈጣሪያች መካከል ከባድ ትግል ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ብልጭ ድርግም፡ ብቅ ጥልቅ፡ በገ ደብዘዝ የሚለው፡ ባንድ በኩል ሲገል በሌላ በኩል የቀዘቀዘ በመምሰል ውስጥ ውስጡን እንደእሳት የሚንበገበገው የመደቦች ትግል ከአለፈው የካቲት ወር ጀምሮ ኢትዮጵያን በሙሉ በማናወጽ ላይ ይገኛል፡፡

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ―ሰራተኛው፡ ደሃውና ጪሰኛው ገበሬ፡ ዝቅተኛው ነጋዴ፡ ጠባቂና ባለእጁ፡ ዝቅተኛው የመንግስት ሰራተኛ፡ ወታደሩ፡ የቀን ሰራተኛውና ኩሊው፡ ሰራአጡ፡ ተማሪው ምሁሩ ወዘተ.― ትግሉን በማፋፋም ላይ ይገኛል፡፡ ጨቋኞችና በዝባዦች ―ንጉሳውያን ቤተሰብ፡ መሳፍንትና ታላላቅ ባላባቶች፡ ባለብዙ መሬቶች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖችና የጦር አለቆች፡ የውጭና የአገር ውስጥ ከበርቴዎች፡ የእነዚህ አጫፋሪዎችና ደላሎች ወዘተ.― በሕዝቡ እንቅስቃሴ በመወጣር ላይ ናቸው፡፡ ሰፊው ሕዝብ ጠላቶቹን በሃይል አጥቅቶ ወደ ሁዋላ እንዲያፈገፍጉ ቢያደርጋቸውም ደምጥማጣቸውን በማጥፋት ዋናውን ድል ገና አልተቀዳጀም፡፡

ታፍኖ፡ መተንፈሻ አጥቶ፡ ተጨቁኖ ተይዞ ስለነበረ ሰፊው ሕዝብ ደንበኛና አጠቃላይ ፀት ገኣ ድርጅት ለማቋቋም አልቻለም፡፡ አሁንም በዚያም በዚህም፡ በልዩ ልዩ አገጣጣ ለመደራጀት ትልቅ መፍጨርጨር በማድረግ ላይ ቢሆንም ትግሉን በግንባር ቀደምነት የሚመራ ተራማጅ የሆነ ጠንካራ ድርጅት ለመመስረት ብርቱ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ከባድ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የድርጅት አስፈላጊነት የማያጠራጥርና የማያከራክር ነው፡፡ ሰፊው ሕዝብ ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ ደምስሶ የመንግስትን ስልጣን ለመቀዳጀት ያልቻለው እንደዚህ አይነት ድርጅት በማጣቱ ነው፡፡ በዚሁ ምክንያት ሳይሆን ይቀራል ባሁኑ ጊዜ ወታደሩ ቀደሚያውን ይዞ የሚገኘው?

ወታደር ከሕዝብ አብራክ የወጣ: የሕዝብ አካል: በተመደበበት ስራ በሚለብሰው ዩኒፎርምና በሚይዘው መሳሪያ እንጅ በሌላው ሁሉ ከሰርቶአደሩ: ከአርሶአደሩና ከሌላው የሰፊው ሕዝብ ክፍሎች በምንም አይለይም:: አባቱ እናቱ ወንድሙ እህቱ ሚስቱ ልጁ አጎቱ አክስቱ እነዚህ ሁሉ: ግማሹ ሰራተኛ: ግማሹ ገበሬ: ግማሹ ተማሪ: ግማሹ ነገደአዳሪ: በአጠቃላይ የሰፊው ሕዝብ ክፍል ናቸው:: ከእነዚህ ከቤተሰቦቹ ጋር የተጨቆነ የተበደለ ግፍ የተሰራበት በመሆኑ የኢትዮጵያ ወታደር በሰፊው ሕዝብ እንቅስቃሴ ውስጥ ከሕዝብ ወገን በመሆን ተሳትፎአል:: የሰፊውን ሕዝብ ትግል አቀናብሮ የሚመራ አጠቃላይና ጠንካራ ድርጅት ባለመኖሩ ለጊዜው ይህ ተግባር በወታደሩ ትከሻ ላይ እንዲወድቅ ሆነ::

የሕዝቡን ፍላጎትና ጥያቄ በመከተል ወታደሩ እነአክሊሉ ሃብተወልድን: እነአንዳልካቸው መኮንንን: እነአስራተ ካሳን: በትውልድ በሃብት በስልጣን ሰፊውን ሕዝብ በመጨቆንና በመበዝበዝ ቀንደኞች የነበሩትን ይዞ አሰረ:: የእነዚህ ሁሉ በላይና ቁንጮ የሆኑትን አጼ ሃይለስላሴንም የፈላጭ ቆራጭ ስልጣናቸውን ቆረጠ፤ የሰይጣናዊ ድርጊታቸው መሳሪያ ከሆኑት ባለሟሎቻቸው ለይቶ ብቻቸውን አስቀምጦአቸዋል:: በሕዝቡ ላይ የደረሰውን ግፍና በደል: የተፈፀመውን ጭቆናና ብዝበዛ በራዲዮ በጋዜጣና በሌሎችም የዜና ማሰራጫ መሳሪያዎች በማብራራትና በመዘርዘር ብዙ ሰርቶአል:: እነዚህና ሌሎችም ከሕዝብ ፍላጎትና ጥያቄዎች ጋር የተያያዙት ድርጊቶች የሚደገፉ ናቸው:: ከየቦታው የሚጎርፈው የሕዝብ ተባባሪነትና ድጋፍ የማያጠራጥር ምስክር ነው::

ወታደሩ የሕዝቡን ፈቃድ እንዲፈጽም <u>ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከውስጡ መርጦ ያቋቋመው ደርግ</u> ግን ገና ወደፍሬነገሩ አልገባም:: ከዚህ በላይ የተመለከቱትና እስካሁን በመፈፀም ላይ ያሉት በቀዳሚያ መደረግ ከሚገባቸው ብዙ ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው:: ዋናዎቹና አጣዳፊዎቹ የሕዝብ ጥያቄዎች ገና ምንም አልተነኩም፤ እንደአሉ ናቸው፤ ጪሰኛና ባለመሬት: ሰራተኛና አሰሪ: ሰፊው ሕዝብና ገዥው መደብ አሁንም እንደተፋጠጡ ናቸው::

ደርጉ ለምን እስከአሁን ወደፍሬ ነገሩ አልገባም? አጣዳፊ ዋናና መሰረታዊ የሆኑትን ጉዳዮች ለምን ቸላ አላቸው? ምንድነው የሚጠብቀው? ችግሩ ምንድነው? 'ሶስተኛ ዙር' ከተጀመረ ወደሁለት ወር ያህል ሲሆነው እስካሁን ድረስ ባለስልጣኖችን ከመያዝና ከማሰር እምብዛም አልፎ ያልሄደው በምን ምክንያት ነው? ይህን ያህል ዝግታው መጉተቱ መጠንዛቱ መንዛዛቱ ለምን ይሆን? 'ደም እንዳይፈስ' በማለት ይሆን? የማን 'ደም'? የሰፊው ሕዝብ ደምማ ሁልጊዜ እንደጎርፍ ይፈስስ የለም? 'በጥንቃቄ: በትእግስት: በአስተዋይነት: በብልህነት' አርአያ ለመሆን፤ 'የአለምን አድናቆት' ለማግኘት ይሆን? የቱ ነው የሚቀድመው? መቅደም የሚገባው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨባጭ ችግር ነው ወይስ 'አለም በብልህነቴ በአስተዋይነቴ' ያደንቀኛል: ምሳሌ ያደርገኛል የሚለው ከንቱ መመፃደቅ: የቅዠት ህልም? ደርጉ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምን መልስ እንዳለው አናውቅም:: ሰፊው ሕዝብ ወታደሩም ጭምር በጉዳዩ ላይ በጣም ማተኮር ያለበት ይመስለናል::

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ደርጉ አንዳንድ ደህና: ከሕዝብ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ጋር የተያያዙ: ነገሮች ቢያደርግም፤ አንዳንድ አድሃሪና ፀረሕዝብ ድርጊቶችንም ፈጽሞአል:: ባንድ በኩል የፖለቲካ ስደተኞች ወደአገራቸው እንዲመለሱ: የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ተደረገ:: መልካም ነው ብሎ ሁሉም ተደሰተ:: በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ተራማጆችንና የሕዝብ ወገኖችን ከመካከሉ ጭምር አሰረ:: በጭቆና ምክንያት ትግል የጀመሩት ኤርትራውያንና ሌሎች ግን 'አገር ለመከፋፈል' በሚል ዘይቤ እንዳይፈቱ ተደረገ:: የሚያሳዝን ትልቅ የፖለቲካ ስህተት ነው:: ሃያ የሚሆኑ ኤርትራውያን የፓርላማ አባሎች ስራቸውን ለቀቁ:: እውነተኛ ነፃነትን ፈላጊዎች ከእስር ቤት ወጥተው ሳያልቁ: እንዲያውም እንዳይወጡ ተከልክለው እያሉ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሲአይኤ ባልደረባ የሆነውን አወናባጁን ሰላይ ስዩም ስብሃትን በራዲዮና በጋዜጣ ሕዝቡን እንዲያወናብድ ፈቀደለታል::

የደርጉ አሰራር በፍፁም የተማታ ነው:: ባንድ በኩል እነአክሊሉንና እነአንዳልካቸውን ከስልጣን አስወግዶ: ቀንደኛ ከሆኑት ገብረአበሮቻቸው ጋር ማረፊያ ቤት በማስገባቱ የሰፊውን ሕዝብ ድጋፍ ሲያገኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የመሳፍንት ወገን የሆነውን እዚህ ግባ የማይባለውን

ሚካኤል እምሩን ጠ/ሚኒስትር አደረገ:: ሌሎችም በሕዝብ ላይ ብዙ በደልና ግፍ የፈፀሙ ባለስልጣኖች አሁንም በስልጣን ላይ ናቸው:: በየጠቅላይ ግዛቱ:በየሚኒስቴሩ:በልዩ ልዩ መንግስታዊ ድርጅቶች ብዙ ብዙ በስልጣን የባለጉ:በማረፊያ ቤት የሚገኙት ባለስልጣኖች ግበረአበሮች አሁንም እንዳሉ ናቸው:: በማስታወቂያ ሚኒስቴር ዜና አሰራጭዎች በተለይ ጋዜጠኞች እንደአስስተ እየተለ የወጡ የማወናበድና ፀረሕዝብ ስራቸውን እንደቀጠሉ ናቸው::

ባንድ በኩል 'ኢትዮጵያ ትቅደም' ማለት የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም ማለት ነው፣ 'መሬት ላራሹ' እያለ የሚያስተጋባው ጪሰኛና ድሃ ገበሬ መሬት እንዲያገኝ ይሆናል፣ ስራ አጥቶ የሚንከራተተው ሁሉ ስራ ይሰጠዋል፣ ሰራተኛው ደንበኛውን የስራውን ዋጋ እንዲያገኝ ይደረጋል፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በእኩልነት ሰባዊና ብሄራዊ መብታቸውን ተጎናጽፈው እየሰሩ ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ይደረጋል፣ ወዘተ. ማለት ነው ተብሎ በመተርጎሙ ሰፊው ሕዝብ ተደስቶ መዝሙሩን አብሮ ያስተጋባል:: በሌላ በኩል ደግሞ:እስከአሁን ድረስ እነዚህን ስራ ላይ ለማዋል ምንም አይነት ፕሮግራም አልወጣም:: ከሕዝቡ በኩል በርከት ያሉ ሃሳቦች:የፕሮግራሙ ንድፎችና ረቂቆች መቅረባቸው አያጠራጥርም:: ቢሆንም ደርጉ የእንዳልካቸውን አጭበርባሪና ፀረሕዝብ መመሪያ ካድሃሪው ከሚካኤል ጋር ባንድነት ባቋቋመው ኰሚቴ ስራ ላይ ለማዋል የቃጣ ይመስላል::

ባንድ በኩል የሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ አለባቸው፣ ደርጉ ይኸንን ለማስፈፀም ነው የተቋቋመው ይላል::በሌላ በኩል ግን ሰላማዊ ሰልፍ ክልክል ነው፣ ማህበራችሁን አፍርሱ፣ አፋችሁን ዝጉ፣ እንቅስቃሴአችሁን አቁሙ፣ ወዘተ. በማለት ደርጉ የሚያደርገው ማስፈራራትና ዛቻ ፍፁም ፀረሕዝብና ፀረዲሞክራሲ ነው:: በጦሩም ውስጥ የደርጉ አባሎች በመጀመሪያ ባልተጣራና በችኮላ ተመርጠው የመጡ በመሆናቸው ተግባራቸውን በሚገባ አልፈፀሙም፣እያንዳንዱ ክፍል ወኪሎቹን እንደገና እየመረጠ ይላክ፣ በማለት የቀረበውን ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ 'ምስጢር አውቋል፣ የስራ ለምድ አገኝቶአል' ወዘተ. በማለት የቀረበው የስልጣን ጉጉት መጋረጃ አንካሳ ምክንያት ነው::

ደርጉ እነዚህን የመሳሰሉ:እርስበርሳቸው የተወናበዱና የተጭበረበሩ ድርጊቶችን መፈፀሙ ከትልቅ ጥርጣሬ ላይ ሳይጥለው አይቀርም:: የኮንጉን ዘማቾች ሲተች/ሲያስፈራራ/ ደርጉ 'እኛ ከሌለን የአገሪትዋ ደህንነት የለም' ሲል ምን ማለቱ ይሆን. 'ደርጉ ኢትዮጵያ ነው፣ ኢትዮጵያም ደርጉ ነች' ማለቱ ከሆነ ቶሎ መታረም የሚገባው የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው:: ኢትዮጵያ የጥቂት ሰዎች ሞኖፖል ሆና ቆይታለች:: አሁን ግን ሰፊው ሕዝብ 'በቃ አቁም፣ ኢትዮጵያ የሰፊው ሕዝብ ጭምር ናት፣ እኛም ኢትዮጵያውያን ነን:: ሁላችንም በደስታዋም ሆነ በችግርዋ ለመካፈል፣ ለሕዝቡ የሚስማማውን አስተዳደርና ሌላም ነገር ለማሰብና በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ መብት አለን፣ በዚህ ረገድ ማንም ከማን አይበልጥም' ብሎአል::

በመውደቅ ላይ ያለው የመሳፍንትና የባላባቶች መንግስት የበላይ ጠባቂና ደጋፊ የሆነው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ትልቅ ሴራ በመጠንሰስ ላይ ነው:: ባሁኑ ጊዜ አንደኛው ቀንደኛ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጠላት የአብዛኛውን የአለም ታዳጊ ሕዝቦችን ደም የሚመጥጠው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሆኑ አያጠራጥርም::

ሲአይኤ የሚባለው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የስለላ ድርጅት በአገራችን ውስጥ ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምሮ መልምሎ ያሰማራቸው ሰላዮች ቁጥር በጣም ብዙ ነው:: አማካሪያች:አዋቂያች: አስተማሪያች:'የሰላም ጓድ' ሰራተኞች ወዘተ. በማለት በየመንግስቱ መስሪያ ቤትና በየድርጅቱ ብዙ የስለላ ሰራዊት አሰማርቶ ብዙዎቻችን የአገር ተወላጆች በገዛ አገራቸውና ሕዝባቸው ላይ እንዲሰለሉ በገንዘብ ገዝቶአቸዋል:: እንደስዩም ሰብሃት:ሳሙኤል አለማየሁ/አአዩ/ እና ሌሎችም አለን አለን የሚሉ አድርባዮች የፀረሕዝቡ የሲአይኤ ቡችሎች መሆናቸውን በማያጠራጥር አኳሃን የሕዝብ ወገኖች ደርሰውባቸዋል:: ከየካቲት ወዲህ የሰፊውን ሕዝብ እንቅስቃሴ ለማጨናገፍና ፍፁም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የሆነ መንግስት ለማቋቋም:ቡችሎቹን ስልጣን ላይ ለማውጣት ምርጥ ሰላዮቹን ወደዚህ በመላክ ከባድ ጥረት በማድረግ ላይ ነው:: አንዳንዶቹ ደርጉ ውስጥና በደርጉ አካባቢ የሚያጨበጭቡትና እምቢልታቸውን የሚነፉትም የሲአይኤ አሻንጉሊቶች መሆናቸው አያጠራጥርም:: ሌሎችም ከስልጣን እርካብ ላይ አንዱ እግራቸውን አውጥተው ወዲያ ወዲህ

በመመለከት ላይ ናቸው፣ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከርቻው ላይ ለመውጣት መሞከራቸው አይቀርም:: የሲአይኤ መርዝ ስር ሰደአል::

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ማድረግ አለበት.

1. አይኑን ከፍቶ ሁኔታውን በንቃት መከታተል፣ በልዩ ልዩ መንገድ በትግሉ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ፣

2. ማህበር እድር ወዘተ. የመሳሰሉትን የህብረትና የአንድነት መሰረቶች በየመስሪያ ቤቱና በየሰፈሩ ማቋቋሙን በመቀጠል ጠላቶችን የማቋቋምበትንና ተንከላቸውን የሚያከሽፍበትን ዘዴ ባንድነት መፈለግ፣

3. በቀበሌ በወረዳ በአውራጃ በጠቅላይ ግዛት:በሙያ ወዘተ. ደረጃ አጠቃላይ የህብረትና የአንድነት ማህበሮችንና ድርጅቶችን ማቋቋም፣ ያሉትንም ማጠንከር፣

4. ትሉ ብሉ አንድ ሁሉንም የሚያጠቃልል ብሄራዊ ግንባር ቀደም የትግል ድርጅት ማቋቋም፣

5. ከልዩ ልዩ የሰፊው ሕዝብ ክፍሎች ተወክለው በሚመጡ የሚመረጥና በቁጥጥራቸው ስር ሆኖ የሕዝብን አጣዳፊ ጉዳዮች እያከናወነ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እንዲቋቋም የሚሰራ አንድ ጊዜያዊ መንግስት እንዲቋቋም መታገል፣

6. እስከዚያው ዘንድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሲቪሎችና ወታደሮች ያሉበት አንድ ደርግ ውሎ ሳያድር ተቋቁሞ በቁጥር 5 ስር የተመለከተውን እንዲያስፈጽም አጥብቆ መጠየቅ ያስፈልጋል::

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ህይወቱንና እድሉን ለማንም አሳልፍ መስጠት አይገባውም:: ባንዳንድ ጥቃቅን ድርጊቶችና በከንቱ የቃላት ተስፋ መርካት የለበትም:: ሙሉ መብቱንና ነፃነቱን ለማግኘት:ጥቅሙን ለማስጠበቅ:ጥያቄዎቹና ፍላጎቶቹ እንዲሟሉ ለማድረግ ታጥቆ ባንድነትና በቆራጥነት በመደራጀት ትግሉን መቀጠል አለበት:: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የአገር ውስጥ ቡችሎቹ በቀላሉ የማይመለሱ ጠላቶቹ መሆናቸውን ተረድቶ በንቃት እንዲጠብቃቸው፣ ሴራቸውንም እንዲያከሽፍ ያስፈልጋል::

እድላችንን በእጃችን እናስገባ
በትግሉ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንሳተፍ::

## የፈላጭ ቆራጭ ነጋሲ የ57 አመት ግፍ

'አባብ ገደል:ከነበትሩ ገደል'በሚል እርእስት ከማርቆስ መንክር የተዘጋጀው የአጤ ሃይለስላሴ አጭር የህይወት ታሪክ እንደሚያስረዳን አጤ 'ራሳቸውን በጣም የሚያፈቅሩ:የራሳቸውን ከንቱ ስራ በሚከፍሏቸው ጋዜጠኞችና ታሪክ ፀሃፊዎች በጉ አስመስለው እያስፀፉ የሚኖሩ:ስማቸው በኢትዮጵያ እንደአምላክ:ከነገስታትች ስም በላይ ከፍ ብሉ እንዲታይ የሚጥሩ ሰው ናቸው'ይለናል በስማቸው የሰየሙት መንገድ:አደባባይ:ሲኒማ ቤት:ትምህርት ቤት:ከተማና ድርጅት ሲቆጠር ራስ ወዳድነታቸውን በግልጽ ያሳያል:: ራሳቸውን በጣም አድርገው የሚወዱ ስግብግብ ሰው ናቸው:: ከራሳቸው እኩል የሚያፈቅሩት ነገር ቢኖር ምናልባት እድሜያቸውን ሙሉ ሲያከማቹት የኖሩትን ገንዘብ ይሆናል:: ምናልባት በሶስተኛ ደረጃ በልጅነታቸው ያሳደጉአቸውንና ዛሬም የሚደገፏአቸውን ለአልጋወራሽነትና ለንጉስነት ያበቁአቸውን የፈረንሳይ ከዚያም የእንግሊዝን ኢምፔሪያሊስቶች ሳይሆን አይቀርም::

አጤ ሃይለስላሴ በአልጋወራሽነታቸው ዘመን ማተሚያ ቤት:ጋዜጣ:ሆስፒታል በማቋቋም ንግድ ጀመሩ::በአገሪቱም ውስጥ ያለአግባብ በመበልፀግ የመጀመሪያው በመሆን የልዩ ልዩ ሸቀጦችን ንግድ በሞኖፖል ከባእድና ከአገር ውስጥ ከበርቴዎች ጋር በመሻረክ ጀመሩ:: ከብሪት:አልኮል:ጋዝ:አምሌ ጨው:ሆቴል:ታክሲ ጭምር የርሳቸው ሞኖፖል ሆነ:: ከሚስታቸውና ከዋና መኳንንቶቻቸው ጋር በዚህ ንግድ ተሳታፊ ሆኑ:: የአገር ነጋዴዎችን አቀርቀዘው በውጭ ነጋዴዎች አገሪቷን አስያዙ:: ከ1920 ዓ.ም.ጀምሮም 'የባንክ ኦፍ አቢሲኒያ'ባለቤት ሆኑ:: ሸሽተው ውጭ አገር በነበሩበትም ዘመን የአገርን ሃብት ለግላቸው ማዋል አለማቀማቸውን የማርቆስ መንክር

ጽሁፍ ያስረዳናል:: የየሩሳሌምን ገዳም ለመሸጥ ማቀዋላቸው በእንግሊዞች ተገልጿል:: እንግሊዞችም ከመለሱአቸው በሗላ የአደላን ወርቅ በመዝረፍ፣ የሕዝቡን መሬት ነጥቀው ቤተርስት ብለው በማቋቋም ለልጆቻቸውና ለጋብችቻቸው የሕዝቡን መሬት በማከፋፈል፣ ጣልያን የሰራውን መንግስት ተረክበው የነበረውን ንብረት በቀዳሚያ ለራሳቸው ከዚያም ለልጆቻቸው: በተለይ የርሳቸውን የንዋይ ፍቅር ለወረሰቸው ለተናኘወርቅ አከፋፍለው የተረፈውንም ለመኳንንቶቻቸው ረጭተዋል:: ይህውን መንግስት እያደኸዩ እርሳቸውና አሽከሮቻቸው እንዲከበሩ አድርገዋል:: በቀርቡም አለፈው ተርፈው ደኑንና መንግስት ያለማውን ሸለቆ ለልጆቻቸውና ለአማቾቻቸው አድለዋል:: በጥቅምት 1948 ዓም ደግሞ ይህን ዘረፋ ለማጽደቅ ህገመንግስት አወጣሁ ብለው የአገሪቱን ሃብት የማደልን መብት ለንጉሱ ሰጥተዋል::

ሞኖፖል እያደረጉ መያዝን ቀደም ብለው ተጠቀመውበት ጊዜው ሲያልፍበት እንደተውት ሁሉ የሕዝብን ንብረት መቀማትንም ከታህሳስ ወዲህ በይፋ ማድረጋቸውን ለመኳንንቶቻቸው የተው ይመስላል:: ታዲያ ህገወጥ ንግድ መተዋቸው ሳይሆን ንብረታቸውን ወደውጭ ስላሸገሩ የብዙ ፋብሪካ ባለቤት በመሆናቸው ነው:: እርሳቸው ታዲያ በሃገር ውስጥ የተጠቀሙት በእጅአዙር ጉብ ነበር:: አለባሹ: ነፍስአባቱ: አቃቤቶቹ: እልፍኝ አስከልካዩ: የግቢ ሚኒስትሩና የጽህፈት ሚኒስትሩ ዋናው ሰራቸው የውጭም ሆነ የሃገር ውስጥ ከበርቴ ፋብሪክ ሲያቋቁም ለአጼ የሚገባ ጉቦ እንዲከፈል ማድረግ ሆነ:: ማስረጃ ይባል ይሆናል:: ማስረጃውን በመርዝ ተገድለው ካለቁት ባለሟሎች የተረፉት 4ኛ ክፍለጦርን ያጣበቡት ባለሟሎቻቸው ያቀርቡ:: አጤ ለጉቦ ደረሰኝ አይሰጡም:: ደረሰኝ ያለው ቢኖር ለ80 አመት የልደት በአላቸው የተሰበሰበው ወርቅ ብቻ ነው:: በዚህ ዘረፋና በውጭ ንግዳቸው ዛሬ ከአስር ቢልዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት አፍርተዋል::

ይህንን ውንብድናቸውን የተቃወሙ አገርወዳድ ኢትዮጵያውያን: ባይቃወሙም ታዘበው ከዝርፊያው ያልተካፈሉት በመርዝ በጥይት ተጨረሱ፣ በግዞት ተንገላቱ፣ በእስር ቤት ማቀቁ:: ታከለ ወልደሃዋርያት: ሎሬንዞ ታእዛዝ: መኩንን ደስታ: አገኘሁ እንግዳ: ዮሃንስ ረምሃ: እጓለ ሃይሉ ክብረት ማሞ መዘምር: ጥላሁን ገዛው....ሸረ ስንቱ በእንደዚህ አለቁ:: በዘወርዋራ መንገድ በነፀሃዩ እንቅስቃሴ: በአባ ሃና ጅማ: በአሉላ በቀለ አፋኝ ጓደኞች ብዙ ሰዎች ተፈጁ፣ ቀጥራቸው ገና ያልታወቀ ብዙ አገርወዳደር አለቁ:: የየካቲ ንቅናቄ ያወጣቸው እነአለቃ ፈጠነ ብዙ ይነግሩን ይሆናል::

በአገር ውስጥ ዘረፋ: ውንብድና: ሕዝብን በመርዝና በጥይት መጨረስ: በእስራትና በግዞት መፍጀት ወና የአስተዳደራቸው መሳሪያ ሲያደርጉ በውጭ ፖለቲካ ደግሞ ሰያቋርጡ የምእራባውያንን የባርነት ጥላ መሳሪያቸው አደረጉ:: ስለአጼ አስተዳደግ የፃፉ አንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር እንደገለፁት ፈረንሳዮች በሀረር በነበረአቸው ሚስዮናውያን በኩል ለአውሮፓ የመንፈስ ተገዥ እንዲሆኑ አድርገው አሳደጓቸው ብለዋል:: እንግሊዞችና ፈረንሳዮችም በመተባበር ልጅ ኢያሱ ወደጀርመንና ቱርክ መንፈሳቸው ስለአመራ /ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ ቢባልም/ እኛኛውን ፈንቅለው እኒህኛውን እንዲያነግሱ የሸዋን መኳንንት በገንዘብ ገዙ:: አጼም እንግሊዝ አገር ሸሽተው እስከሄዱበትም ጊዜ ድረስ ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ ጋር የግል ንግዳቸውንና የሃገሪቱን ፖለቲካ አስተሳሰሩ:: የሌላ አገር መሪያች የመሳሪያ ፋብሪካ ለማቋቋም ስንት የለፉ ሲሆን አጤ ሃይለስላሴ ያቋቋሙት የግላቸው የሆነ የቢራ ፋብሪካ ብቻ ነው:: ለአገሪቱዋ በጣም አስፈላጊ የነበረውን የጦር መሳሪያማ በግዥም ሳያስመጡ ማይጨው ደረሰ:: ማይጨውም ላይ ሕዝቡ 'እንዳይዘጋጅ መሳሪያ ለማግኘት ባለመቻሉ በጣልያን ጦር ተጨፈጨፈ:: የጣሊያኑ ጄኔራል ባደልዩ እንደገለፀው 'የአበሻን ጦር ለብዙ አመታት መዋጋት ይኖርብናል ብለን ተዘጋጅተን ነበር:: ነገር ግን ተፈሪ ጦሩን ሳያዘጋጅ በማቀየቱና ስንቅ ከልክሉ እንዲራብ በማድረጉ : የተማሩ ወጣቶች የደፈጣ ጦርነት ይደረግ ያሉትን ሃሳብ ትቶ የመሳፍንትን አሮጌ ሃሳብ በመከተሉና የጦር አዛዥነት ችሎታ የሌለው በመሆኑ የሃበሻን ጦር መሪ አሳጣው:: ስለዚህም በቀላሉ ፈታነው' ብሏል::

አጤ ሃይለስላሴ ባልነበረበት በተምቤንና በደቡብ ግንባር በቻ ውጊያ ተደርጐ ማይጨው ላይ ሕዝቡ
ለመከላከል ሳይችል በጢስና በረሃብ አለቀ:: በማንም አገር በጦር ፍርድ ቤት የሚያስጠይቅ
በደል ያኔ ፈጸመዋል::/በ1943 እነቢትወደድ ነጋሽ:እነአለቃ ፈጠነ ከተነሱበት አንደኛው
ምክንያት ለምን ሳንዋጋ በቀላሉ ተሸነፍን በማለተ ሃላፊውን ይዞ ለጦር ፍርድ ቤት ለማቅረብና
ለመቅጣት ነበር:: የመቶ አለቃ በቀለ አናርጮስ በቀደም አለተ በራዲዮ በተናገሩ ጊዜ ይህንን
ነው ያሰሙት::/ አጤ ለምን አልተዋጉም? ምክንያቱም በፈረንጆች ስለሚያምሉኩ ከመዝመታቸው
በፊት እንሸነፋለን የሚል እምነት ስላደረባቸውና ስለፈሩ ለመከላከልም ፈቃደኛ አልነበሩም::
በቅርቡ የተከፈተው የእንግሊዝ መንግስት አርሺቭ እንደገለፀው እርሳቸው በዚያን ጊዜ ከእንግሊዝ
ጋር አባካችሁ በቅኝ ግዛት ጥገኝነት/ኘሮቴክቶሬት/ ያዙን እያሉ ይሳሳኩ ነበር:: እርሳቸው
ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ስር ብትወድቅ አልቸገራቸውም:: ያንን መከረኛ ዘውድ ካለወሰዱባቸው ለሌ
ላው ምን ግድ ኖሮአቸው:: ጣልያን ዱል በሆነም ጊዜ የእንግሊዝና የደቡብ አፍሪቃ ጦር ኢትዮ
ጵያን ይዞ አለለቀ ቢል አጤ ሃይለስላሴ ተስማምተው ነበር:: እንዲወጡ ያደረጉት አርበኞቹ
ና ቸው:: ጣልያን የተከላቸውን ፋብሪካዎች እንግሊዝ እየነቀለ ሲያግዝ አገርወዳድ የሆኑ ሰዎች
ቢቃወሙ ንጉሱ ተከታይ እየላኩ አስፈራርተዋቸዋል:: እንግሊዝ እንደፈለገ እንዲያደርግ እርሳ
ቸው አበረታተዋል:: በምስራቅ ኢትዮጵያም በቆየበት ጊዜ ነጮና ጥቁር ለምን ይለያል ብለው
የተቃወሙ አገርወዳዶች በአጤ ሃይለስላሴ ፖለቲካ አበላሻችሁ እየተባሉ ማስፈራሪያ ይሰጣቸው
ነበር:: ኤርትራንም ከእንግሊዝ ነፃ ለማውጣት የታገሉትን አገርወዳዶች አጤ እያስለቀሙ ወደግዞት
አስልከዋል:: በአምስቱ አመታት የጣልያን ባንዳ የነበረትን እነአበበ ገመዳን:እነመኮንን ደነቀን
እነብላታ አይማሩን እንዳስጠጉ ሁሉ በኤርትራም የእንግሊዝ ወገን የነበረትን እነተሰፋዮሃንስን
ሸመዋል:: አርበኞቹን አርቀዋል:: ዛሬ እንኳን በጅቡቲ ወደብ ጉዳይ ከፈረንሳይ ጋር የሚያደር
ጉት የስውር ስምምነት የዚሁ ከቅኝ ገዥዎች ጋር መስማማት ውጤት ነው:: እንደአ.አ. መስከረም
7/51 ጥር 16/51 ግንቦት 22/53 ሚያዝያ 25/57 አጤ ሃይለስላሴና አክሊሉ ሃብተወልድ
ከአሜሪካን ጋር የተፈራረሙአቸው የጦር ስምምነቶች ኢትዮጵያን ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የእጅ
አዙር ቅኝ ግዛት በማድረግ የጦር ማስፈሪያ አድርገዋታል፣ ማእድኗንና ማንኛውንም ሃብቷን ያለ
ምንም ገደብ የአሜሪካን የጦር ስንቅና መጠቀሚያ አድርገውታል:: እነኝህ ስምምነቶች የአጤ
ሃይለስላሴን የ57 አመት የቅኝ ገዥዎችና የኢምፔሪያሊስቶች መሳሪያነት በይፋ እንዲታወቅ አድር
ገዋል::

ያለአግባብ መበልፀግ ጀማሪና አስጀማሪው አጤ ራሳቸውን ከህግ በላይ አድርገው ህጉን
አስተዳደሩን የራሳቸው ስም ማጋነኛ የራሳቸው ንብረት መዳበሪያ አድርገው ኖሩ:: ከፍ ያለ የአ
ስተዳደር በደል በሕዝቡ ላይ አደረሱ:: የኢትዮጵያውያን ላብ ያፈራውን ንብረት በውጭ አገር
አስቀመጡ:: ለጣልያን ለፈረንሳይ ለእንግሊዝ ይበልጡን ደግሞ ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች አገሪ
ትዋን ሸጡ:: ማስረጃው ሞልቶአል:: ምስክሩ ተርፎአል:: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይፋረዳቸዋል::

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::